**የ 2013 የትምህርት መጀምርያ በአል አያምልጥዎት**

ቅዳሜ ኦገስት 24 ከ 11 a.m. -2 p.m በ Carver Educational Services Center, 850 Hungerford Drive Rockville የሚከናወነው የትምህርት መጀምርያ በአል አያምልጥዎት። በሙዚቃ፣ በመዝናኛዎች፣ በልጆች እንቅስቃሴዎች፣ ስጦታዎችና ሌላም ሌላም እየተደሰቱ፣ የትምህርት አመት መወንጨፍያ የደመቀ ከውኅት እንዲያስተውሉና ስለትም/ቤት ስርአት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች እንዲማሩ፣ ሁሉም የ MCPS ተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው ተጋብዘዋል!

እባክዎን በዚህ አመት በአሉ ላይ የጀርባ ቦርሳዎች እንደማይታደሉ ይወቁ፣ ለችግረኛ ተማሪዎች እንዲሰራጩለ ተወሰኑ ትም/ቤቶች ይሰጣሉ።

ከ 10:30 a.m. ጀምሮ በሚከተለው ከተዘረዘሩት ትም/ቤቶች ወደ በአሉ የአውቶቡስ ደርሶ-መልስ መጓጓዣ ይቀርባል፡ - Shady Grove MS, Watkins Mill HS, Wheaton HS, Springbrook HS, Richard Montgomery HS, Rockville HS, Northwest HS, Kennedy HS, Einstein HS, Blair HS, Seneca Valley HS, እና Paint Branch HS። የአውቶቡስ ደርሶ መልስ ጉዞዎች ከ 10:30 a.m. and 2:30 p.m. ይኖራሉ።

ስለ በአሉ ተጨማሪ መረጃ፣ Back-to-School Fair ድረገፅ ይጎብኙ ወይም Office of Community Engagement and Partnerships (የማህበረሰብ ተስትፎና ሽርክናዎች ፅ/ቤት) በ 301-270-3100 ይደውሉ።

**የትም/ቤት መከፈቻ ቀን ፎቶችዎን ይላኩልን**

Montgomery County Public Schools ወላጆች የሚወዷቸውን የትም/ቤት መከፈቻ በአል ፎቶግራፎች ሰኞ ኦገስት 26 እንዲልኩ ይጋብዛሉ። ወላጆች የልጃ(ጆ)ቻቸውን የላቁ የትም/ቤት መከፈቻ በአል ፎቶ መርጠው በኢሜይል ወደ pio@mcpsmd.org መላክ አለባቸው። ሰኞ ጥዋት ጀምሮ በርካታ ስእሎች በ MCPS ድረገፅ ይለጠፋሉ።

ፎቶ ለማበርከት፣ የሚከተሉትን ቀላል እርምጃዎች ይከተሉ፡

- ከሁሉ የላቀውን አግዳሚፎቶ ይምረጡ
- ፎቶውን በ jpeg ፋይል መልክ (ከ 4 MB ያልበለጠ) በኢሜይል ወደ pio@mcpsmd.org ይላኩ።
- የልጅዎን የመጀመርያ ስም፣ የክፍል ደረጃና የትም/ቤት ስምአክሉበት። (የመጭረሻ ስምአናትምም። )

ፎቶውን በመስጠት፣ በ MCPS ድረገፅ እንዲታተምወላጆች ተስማምተዋል ማለት ነው። ጥያቄዎች ካለዎት፣ Department of Public Information and Web Services (የህዝብ ማስታወቂያና የኢንተርኔት አገልግሎቶች መምርያ) በ 301-279-3853 ይደውሉ ወይም በ pio@mcpsmd.org ኢሜይል ያድርጉልን።

**የወደፊታችንን አብሮ መገንባት**

የ Montgomery County የትምህርት ቦርድ የ MCPS የሚመጡአመታት ስራ የሚመራ አዲስ Strategic Planning Framework (ስልታዊ ፕላን መዋቅር) በቅርብ ግዜ አፅድቋል። መዋቅሩ፣ *Building Our Future Together: Students, Staff and Community (የወደፍታችንን አብሮ መገንባት፡ - ተማሪዎች፣ ማምህራን እና ማህበረሰብ)*፣ የሚያተኩረው ተማሪዎች በ 21ኛው ክፍለ ዘመን ለስኬት የሚያስፈልጓቸውለሶስት መሰረታዊ ክሂሎቶች—ለአካዴሚያዊ ብልጫ፣ የችግር አፈታት ፈጥራ፣ እና ለማህበራዊ ስሜታዊ መማር—እንዲሁምለግብረታዊ ብልጫ ቀጣይ ቁርጠኝነት ነው። መዋቅሩ ተማሪዎች ምን ማወቅ እንዳለባቸውና ምን መስራት መቻል እንዳለባቸው፣ እንዲሁምየትም/ቤት ሰራተኞች፣ ወላጆች እና የማህበረሰቡ አባላት ተማሪዎችን ለመደገፍ የተወሰኑ ድርጊቶች ማከናወን እንዳለባቸው ይገልጻል። ስለ Strategic Planning Framework (ስልታዊ የፕላን መዋቅር) በተጨማሪ ለማወቅ በ MCPS ድረገፅ ወይምየመዋቅሩ ቅጂ ከአካባቢዎ ትም/ቤት ይውሰዱ።

**መቆጣጠርያ ዝርዝር፡ ላዲሱ የትምህርት አመት ዝግጅት**

ወላጆች፣ ጊዜውእንደገና ደረሰ—ያዲስ የትምህርት ዘመን መጀመርያ! ተዘጋጅተዋል? ስኬታማአመት እንዲሆንልዎ የሚፈልጓቸውን መርጃዎች የሚያስታጥቅ የመቆጣጣርያ ዝርዝር ይህውና፡ -

- ✓ ስለ ትም/ቤት መዝጊያ እለቶች፣ ህመምእና ጠቃሚየቅርብ ክንወኖች ግንኙነት እንዲኖርዎ የልጅዎን **Student Emergency Information Form (የተማሪ አስቸኳይ ሁኔታ መረጃ ቅፅ)**ይምሉ። መረጃዎ በአመቱ ውስጥ ለውጥ ካደረገ ትም/ቤቱን እንዲያሳውቁት እርገጠኛ ይሁኑ።
- ✓ በ **Edline**ይመዝገቡ! Edlineበ ድረገፅ የተመሰረተ የመካከልኛና የ 2ኛ ደረጃ ትም/ቤት ተማሪ ወላጆች የልጃቸውን ክፍሎችና ስራዎች የሚከታተሉበት ስርአት ነው።
- ✓ ይመልከቱ፣ ያትሙወይምከድረገፅ ያውርዱየ **2013-2014 ቀን መቁጠርያ** እናምየዋና ዋና እለቶችና ክውነቶች መረጃ ይኑርዎ።
- ✓ የልጅዎን **ያውቶቡስ መስመር መረጃ**ይኑርዎ። ስለ አውቶቡስ መስመር አቅጣጫዎች ጥያቄ ያላቸውወላጆች መፍትሄ እዚህ ያግኛሉ።
- ✓ ለልጅዎ ሂሳብ ገንዘብ ለመጨምር በ **mylunchmoney.com** መጠቀም ያስታውሱ። ይህ ልጅዎ በየቀኑ ገንዘብ ተሸክሞ ወደ ትም/ቤቱ የመምጣት አስፈላጊነትን ያስወግዳል። የትም/ቤት ምግብ ቤቶች ጥሬ ገንዘብ ወይም የቼክ ቅድሚያ ክፍያም ይቀበላሉ።
- ✓ በልጅዎ ትም/ቤት **የትምህርት መጀመርያ ቀን ምሽት**ይሳተፉ።

**የ MCPS ስርአተ ትምህርት 2.0፡ -ይበልጥ የጠነከረ መሰረት መገንባት**

ባለፉት አራት አመቶች፣ MCPS በኤሌሜንታሪ ትም/ቤት ስርአተ ትምህርት የደመቁ ማሻሻያዎች ሲያደርጉበት ነበር። Curriculum 2.0 ተብሎየ ሚጠራውየ ተሻሻለው ስርአተ ትምህርት የ ተተለመውተማሪዎች መስረታዊ በሆኑት በሂሳብ፣ ንባብ እና በፅሁፍ ጠንካራ መሰረት መቀበላቸውን ለማረጋገጥ ነው። እንደ ማህበራዊ ጥናቶች፣ ሳይንስ፣ አካል ማጎልመሻና ኪነ ጥበብ በመሳሰሉ ሌሎች ዋና ርእሶችም የታደሰ ትኩረትም ያስቀምጣል። በ 21ኛውክፍለ ዘመን ለዘላቂ የትምህርት

ህይወትና ስኬት አስፈላጊ በሆኑት በሂሳዊና የፈጠራ አስተሳሰብ ችሎታዎች ላይ ያሰምራል። ስለ ስርአተ ትምህርት 2.0 እዚህ በተጨማሪ መማር ይችላሉ።

**የ MCPS Parent Academy (የ ቤተሰብ አካዴሚ) ኦጉስት 29 ይጀምራል**

MCPS Parent Academy (የ ቤተሰብ አካዴሚ) ለወላጆችና ለማህበረሰቡ አባላት የልጆቻቸውን የትም/ቤት ስኬት ለመደገፍ መረጃዎች፣ መገልገያዎች፣ መሳርያዎችና ጥቆማዎች የሚያቀርቡ ነፃ አውደ ጥናቶች እንዲከታተሉ እድል ይሰጣል። የፎል ወራቱ አውደ ጥናት፣ ስለ Outdoor Education (የደጅ ትምህርት) ስብሰባ ኦገስት 29 ይጀምራል። ስለ ጤና ማኑሮ፣ የኮምፒውተር ደህንነትና ማህበራዊ ሚድያ፣ እና ስለ ውጤታማ ልጅ አስተዳደግ ስብሰባዎች አያምልጥዎት። የተሟላ የኮርሶች ዝርዝር በ Parent Academy ድረገፅ ይገኛል።

**እለቱን ያስታውሱ፡ - 2013 State of the Schools (የ ትም/ቤቶች ሁኔታ)**

ኖቨምበር 11 በጥዋቱ፣ Superintendent Joshua P. Starr (ዋና ተቆጣጣሪ ጆሹዋ ፒ ስታር) ስለ ትም/ቤቶች ሁኔታ ሁለተኛውን አመታዊ ንግግር Strathmore በሚገኘው የሙዚቃ አዳራሽ ሲያቀርብ ይገኙ። ይህ ዝግጅት ነፃና ለሕዝብ ክፍት ነው። ተጨማሪ መረጃዎች በወደፊት የ MCPS QuickNotes ህትመት መግለጫይሰጥባቸዋል።

**ስለ ተማሪ ዝውውር መምርያ በቀረቡት ክለሳዎች አስተያየትዎን ይስጡ**

የ Montgomery County የትምህርት ቦርድ በ Policy JEE*Student Transfers (የተማሪ ዝውውሮች)* በቀረቡት ክለሳዎች የህዝብ አስተያየት ይፈልጋል። መርሁ Change of School Assignment (COSA) (የ ትም/ቤት ምደባ ለውጥ) የሚለውን የ MCPS ተማሪዎች፣ ከመኖርያ ትም/ቤታቸውወይም ከተመደቡበት Individualized Education Program (IEP) (ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም) ሌላ ለመከታተል፣ የዝውውር ፈቃድ የሚያገኙበትን መመዘኛ ያስቀምጣል። ለዚህ መርህ የህዝብ አስተያየት መስጫግዜ እስከ ሴፕቴምበር 30 2013 ክፍት ይሆናል። ከዚያም የትምህርት ቦርድ የመርህ ኮሚቴ በፎል ወራት አስተያየቱን ሁሉም አባላት ለሚገኙበት ቦርድ ከማቅረቡ በፊት ሁሉንም ህዝባዊ አስተያየቶች ያገናዝባል። በዚህ መርህ የሚደረጉ ማናቸውም ለውጦች በ 2013-2014 የትም/ዘመን በቀረቡ የዝውውር ጥያቄዎች የሚያስከትሉት ሰበብ የለም። የትምህርት ቦርድ የመርህ ኮሚቴ እነ ዚህን የለውጥ ሃሳቦች

ያቀረበውለ COSA (የትምህ/ቤት ምደባ ለውጥ) መምርያ ግልጽነትና የትርጉም ጽኑነት ለማላበስ ነው። ስለ ቀረቡት ለውጦችና እንዴት ሃሳብ መስጠት እንዳሚቻል ለመማር MCPS ድረገፅ ይጎብኙ።

**SSL Hours እስከ ሰፕተምበር 27 ያስገቡ።**

በሰመር ወራት ስለተከናወነ የአገልግሎት ሰነዳቸውን ተማሪዎች MCPS Form 560-51: Student Service Learning Activity Verification (የተማሪ የትምህርት አገልግሎት እንቅስቃሴ ማረጋገጫ) በመጠቀም እስከ አርብ መስከረም 27 ገቢ ማድረግ አለባቸው። የአገልግሎት ሰአቶች በመጀመርያ ሩብ አመት ሪፖርት ካርድ ይንፀባረቃሉ።

MCPS Form 560-50 በመጠቀም SSL በቅድሚያ እንዲፀድቅ የጠየቁ ተማሪዎች ሰነድ ሲያስገቡ የቅድሚያ ማፅደቂያ ቅፅ ከማስመስከርያ ቅጽ ጋር ማያያዝ አለባቸው። ጥያቄዎች? SSL ድረገፅ ይጎብኙ።